የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 25
ADDIS ABABA, 28th April, 2026

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፱/፪ሺ፲፰

ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሶስተኛ ተጨማሪ ብድር ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………..………………..…..ገጽ ፲፱ሺ፮፻፷፭

**Content**

Proclamation No. 1409/2026

International Development Association Loan Agreement for Urban Productive Safety Net and Jobs Project Third Additional Financing Ratification Proclamation …………….......Page 19665

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፱/፪ሺ፲፰

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሶስተኛ ተጨማሪ ብድር ፩፻፹፬ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስዲአር (አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስዲአር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1409/2026

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to One Hundred Eighty Four Million One Hundred Thousand SDR (SDR 184,100,000) for Urban Productive Safety Net and Jobs Project Third Additional Financing was signed on the 7th day of January 2026;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፲፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሶስተኛ ተጨማሪ ብድር ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፱/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7961 -ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፹፬ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስዲአር (አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስዲአር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 12th regular session held on 22nd day of March, 2026;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Urban Productive Safety Net and Jobs Project Third Additional Financing Ratification Proclamation No. 1409/2026".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Credit Number 7961- ET signed on the 7th day of January 2026 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to One Hundred Eighty Four Million One Hundred Thousand SDR (SDR 184,100,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, on this 28th Day of April ,2026**

**ታዬ አፅቀስላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**TAYE ATSKESELASSIE**
**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**